# ለሕዝብ ጥቅማጥቅሞች ያመልክቱ

Legal Aid Society OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

**ይሄ ገጽ የሚገልጸው አንዳንድ የተለመዱ የሕዝብ ጥቅማጥቅሞችን ነው። ለአንዳንዶቹ ወይም ደግሞ ለሁሉም ጥቅማጥቅሞች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።**

**እንዴት ማመልከት እንደሚችሉ ለማወቅ ቀጣዩ ገጽ ላይ ይሂዱ።**

## SNAP፣ TANF፣ እና የሕክምና ድጋፍ

ማግኘት የሚችሉት የመጨረሻው የ **SNAP** መጠን እንደ ቤተሰብዎ መጠን ነው፡-

| የቤተሰብ ብዛት | SNAP ሊያገኙ የሚችሉት የቤተሰብዎ ወርሃዊ የገቢ መጠን ከዚህ ካነሰ ነው… | *የመጨረሻው ወርሃዊ የጥቅማጥቅም መጠን* |
|---|---|---|
| 1 | $1,064 | $234 |
| 2 | $1,437 | $430 |
| 3 | $1,810 | $616 |
| 4 | $2,184 | $782 |
| 5 | $2,557 | $929 |

ማግኘት የሚችሉት የመጨረሻው የ **TANF** መጠን እንደ ቤተሰብዎ መጠን ነው፡-

| የቤተሰብ ብዛት | TANF ሊያገኙ የሚችሉት የቤተሰብዎ ወርሃዊ የገቢ መጠን ከዚህ ካነሰ ነው… | *የመጨረሻው ወርሃዊ የጥቅማጥቅም መጠን* |
|---|---|---|
| 1 | $574 | $414 |
| 2 | $675 | $515 |
| 3 | $818 | $658 |
| 4 | $964 | $804 |
| 5 | $1,088 | $928 |

እንደ ገቢዎ መጠን እና የቤተሰብዎ ብዛት መሰረት እርስዎ እና ቤተሰብዎ ለ **ሜዲኬድ ወይም አሊያንስ** የኢንሹራንስ ሽፋን ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። *ምንም እንኳን የቤተሰብዎ የገቢ መጠን ከላይ ከተጠቀሰው በላይ ቢሆንም ልጆችዎ እና እርጉዝ ሴቶች ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።*

| የቤተሰብ ብዛት | ሜዲኬድ ወይም አሊያንስ ሊያገኙ የሚችሉት የቤተሰብዎ ወርሃዊ የገቢ መጠን ከዚህ ካነሰ ነው… |
|---|---|
| 1 | $2,147 |
| 2 | $2,903 |
| 3 | $3,660 |
| 4 | $4,417 |
| 5 | $5,173 |

## የአካለስንኩልነት ጥቅማጥቅሞች

**አዋቂዎች፡-**

መስራት እንዳይችሉ የሚያደርግ የረጅም ጊዜ የጤና ችግር ያለብዎት ከሆነ፣ የአካለስንኩልነት ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። የአካለስንኩልነት ጥቅማጥቅሞች የሚያካትቱት SSI (ተጨማሪ የደህንነት ገቢ) እና SSDI (የማህበራዊ ደህንነት የአካለስንኩልነት ኢንሹራንስ) ያካትታል።

**ልጆች--**

ልጅዎ የከፋ የረጅም ጊዜ የጤና ችግር ያለበት/ባት ከሆነ፣ SSI ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።



## የስራ አጥነት ኢንሹራንስ

ስራ ያላገኙ ከሆነ እና የእርስዎ ጥፋት አይደለም፣ የስራ አጥነት ኢንሹራንስ ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

**ለማመልከት፣ www.dcnetworks.org ን ይጎብኙ እና "የስራ አጥነት ጥቅማጥቅም ያጠይቁ" የሚለው ትር ላይ ይጫኑ ወይም 202-724-7000 ላይ ይደውሉ።**

በተጨማሪም ከወረርሽኙ ጋር የተያያዙ ተጨማሪ የስራ አጥነት ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ሆኖም ግን፣ እነዚህ ከወረርሽኝ ጋር የተያያዙ መርሀግብሮች ሴፕቴምበር 4 ቀን፣ 2021 ጀምሮ ያበቃሉ። ስለ እነዚህ መርሀግብሮች እዚህ ላይ የበለጠ ለማወቅ ይችላሉ፡- **https://does.dc.gov/service/unemployment-compensation-process**

**እገዛ ይፈልጋሉ?** (202) 628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ https://www.legalaiddc.org/online-intake/።

## ለምግብ ድጎማ፣ ታንፍ፣ ሜዲኬድ፣ እና አልያንስ እንዴት ማመልከት እችላሉሁኝ?

ለእነዚህ ጥቅማጥቅሞች በአንድ ጊዜ ላይ ማመልከት ይችላሉ! ለማመልከት ሁለት ቅደም ተከተሎች አሉ!

**ቅደም ተከተል 1፡- የሚያስፈልጎትን ሰነዶች ያዘጋጁ።** *ኦርጅናሎቹን እንዳይልኩ! በፎቶ ያንሱት ወይም ኮፒ ያድርጓቸው።*

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የእርስዎ የፎቶ መታወቂያ። | የእርስዎ የማህበራዊ ደህንነት ካርድ (ያለዎት ከሆነ) | የገቢ ምንጭ ማሳያ ( ልክ እንደ የክፍያ ማረጋገጫ) | የፍጆታ ክፍያ ደረሰኝዎ ወይም ሌላ የአድራሻ ማረጋገጫ | በቤተሰብዎ ውስጥ ለሚኖሩ እያንዳንዱ ሰዎች የልደት ምስክር ወረቀቶች |

**ቅደም ተከተል 2፡- ያመልክቱ።**

አንድ ማመልከቻ ላይ የምግብ ድጎማ፣ ታንፍ፣ ሜዲኬድ እና ዲሲ የሕክምና አልያንስን ጨምሮ ሁሉም የሕዝብ ጥቅማጥቅሞች ላይ ማመልከት ይችላሉ። ከአራት መንገዶች ውስጥ በአንዱ ያመልክቱ፡-

በአካል በመገኘት? ከእነዚህ አገልግሎት ማዕከሎች አንዱ ላይ ይሂዱ። በሚያመለክቱበት ሰዓት ማረጋገጫ ደረሰኝ ይጠይቁ።

- **አኖክስቲያ የአገልግሎት ማዕከል (Anacostia Service Center)**
  2100 Martin Luther King Jr. Avenue SE
  (202) 645-4614
- **ኮንግረስ ሃይትስ አገልግሎት ማዕከል (Congress Heights Service Center)**
  4049 South Capitol Street SW
  (202) 645-4546
- **ኤች ስትሪት አገልግሎት ማዕከል (H Street Service Center)**
  645 H Street NE
  (202) 698-4350
- *[ተዘግቷል]* **ፎርት ዴቪስ አገልግሎት ማዕከል (Fort Davis Service Center)**
  3851 Alabama Avenue SE
  (202) 645-4500
- *[ተዘግቷል]* **ታይለር ስትሪት አገልግሎት ማዕከል (Taylor Street Service Center)**
  1207 Taylor Street NW
  (202) 576-8000

**በስማርት ስልክዎ፡-** ኦንላይን የመተግበሪያ መደብር ላይ የ **District First** መተግበሪያን ያውርዱ። በስልክዎ ላይ ያመልክቱ። የተሰጥዎትን ማረጋገጫ ቁጥር ጽፈው ያስቀምጡ።

**ኦንላይን፡-** ኦንላይን በዚህ ላይ ያመልክቱ https://dcbenefits.dhs.dc.gov። የተሰጥዎትን ማረጋገጫ ቁጥር ጽፈው ያስቀምጡ። ያስረከቧቸውን ነገሮች ቅጂ ያስቀምጡ።

**በደብዳቤ (የሚመከር አይደለም)፡-** ማመልከቻውን እዚህ ላይ ያግኙ https://dhs.dc.gov/node/117542። አገልግሎት ማዕከል ላይ ማመልከቻውን እና የሰነዱን ቅጂዎችን ይላኩ(ወደ ግራ ተዘርዝሯል)። በማመልከቻዎ ላይ በደብዳቤ እንዳላኩ ያሳውቁ።

## ልክ እንደ SSI እና SSDI ዓይነት የአካለስንኩልነት ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት እንዴት ማመልከት እችላለሁኝ?

**ቅደም ተከተል 1፡- የሚያስፈልጎትን ሰነዶች ያዘጋጁ።** *ኦርጅናሎቹን እንዳይልኩ! በፎቶ ያንሱት ወይም ኮፒ ያድርጓቸው።*

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የእርስዎ የፎቶ መታወቂያ እና የልደት ምስክር ወረቀት | የእርስዎ የማህበራዊ ደህንነት ካርድ (ያለዎት ከሆነ) | ንብረት እና የስራ ታሪክ መረጃ | የፍጆታ ክፍያ ደረሰኝዎ ወይም ሌላ የአድራሻ ማረጋገጫ | በእጅዎ ያለ የሕክምና ማስረጃ |

**ቅደም ተከተል 2፡-** ያመልክቱ። SSI እና SSDI ጨምሮ ለአካለስንኩልነት ጥቅማጥቅሞች፣ በሚከተሉት መንገዶች ማመልከት ይችላሉ፡-

**ስልክ፡-** በስልክ የአካለስንኩልነት ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት የማመልከቻ ቀጠሮ ለ ውሉ።

መደወል ይችላሉ፡-

- የብሔራዊ SSI ቁጥር፡- 1-800-772-1213 (ወይም ከክፍያ ነፃ ስል 1-800-325-0778)፣ **ወይም**
- የእርስዎ የአካባቢ ቢሮ። ቁጥራቸው እዚህ ላይ ማግኘት ይችላሉ

https://secure.ssa.gov/ICON/ic001.action#officeResults።

**እገዛ ይፈልጋሉ?** (202) 628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ https://www.legalaiddc.org/online-intake/።

**ኦንላይን፦** ኦንላይን በዚህ ላይ ያመልክቱ ttps://www.ssa.gov/benefits/disability/#anchor6። የተሰጥዎትን ማረጋገጫ ቁጥር ጽፈው ያስቀምጡ። ያስረከቧቸውን ነገሮች ቅጂ ያስቀምጡ።

**በደብዳቤ (የሚመከር አይደለም)፦** ማመልከቻውን እዚህ ላይ ያግኙ https://www.ssa.gov/forms/ssa-16-bk.pdf። ከእርስዎ ሰነድ ቅጂ ጋር የአከባቢዎ ማህበራዊ ደህንነት ቢሮ ላይ ይላኩት። በደብዳቤ የላኩበትን ማስረጃ ያስቀምጡ።